## ❖ ኩርኮራ ለምን?

**«ከምንም በላይና በፊት፤ እውቀት**
**የተሻለ የማዋለድ አስተዋይነት እና የራስ ፍተሻ ድፍረት ነው»**

***ለዓመታት ወይም ለተወሰነ ወቅት ይዘው የቆዩትን እምነት መፈተሽ ህመም አለው። ድፍረትም ይጠይቃል። ማድረግ መቻሉ ደግሞ በግለሰባዊም ሆነ በማህበረሰባዊ ደረጃ ገንቢ ጠቀሜታ ይኖረዋል።***

**ኩርኮራ፤ ይህን ፈተና ከመገንዘብ የመነጨ፣ ተገቢ ኃላፊነትም ነው በሚል እምነት የተጀመረ ጥረት ውጤት ነው።** ***መነሻና መድረሻውም የፅሑፉ ትኩረት የሆኑ ጉዳዮችን ጨምሮ በሁሉም ዘርፍ ያለንን የግልና የጋራ እምነት በየጊዜው የመፈተሽ ድፍረትና ተግባር ባህል ሆኖ እንዲለመድ እልህ መጫርና ማበረታታት የሆነ ብቻ ነው።***

***እንኮርኩር!... እንኮራኮር!... ኩርኮራ!***